መልእክት አራት

## ጸጋ በጴጥሮስ መልእክቶች ውስጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ጴጥ. 1፡2፣ 10፣ 13፤ 2፡19-20፤ 3፡7፤ 4፡10፤ 5፡5፣ 10፣ 12፤ 2 ጴጥ. 1፡2፤ 3፡18

**I. ጸጋ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ሕይወት እንደሚሰጠው መንፈስ ለእኛ ራሱን በነጻ የሚሰጠው፣ ለእኛ ሁሉን ነገር የሆነው እና ለድሰታችን በእኛ፣ ለእኛና በእኛ በኩል ሁሉን ነገር የሚያደርገው ነው—ዮሐ. 1፡14፤ 16-17፤ 2 ቆሮ. 1፡8-9፣ 12፤ ገላ. 2፡20፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 15፡10።**

**II. የጸጋ መባዛት በየዕለት ሕይወታችን በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ጌታችን ሙሉ እውቀት የሚባዛው ጸጋ ነው፤ በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ጸጋ የበለጠ፣ የሚባዛና የሚበዛ ነው —1 ጴጥ. 1፡2፤ 2 ጴጥ. 1፡2፤ ዮሐ. 1፡16፤ ኤፌ. 1፡6-8፤ 2፡7፤ ሮሜ. 5፡17፣ 21፤ 1 ጢሞ. 1፡14፤ ራእ. 22፡21፦**

ሀ. ጸጋ የሚባዛልን በመከራዎቻችን፣ በጉድለቶቻችን እና በድካሞቻችን በኩል ነው፤ ጸጋ የሸክማችን ተሸካሚ የሆነው ክርስቶስ ነው፤ ሸክሞች ይበልጥ በኖሩን መጠን፣ ክርስቶስን እንደ ጸጋ ለመለማመድ የበለጡ እድሎች ይኖሩናል—2 ቆሮ. 12፡7-9፤ ተዛ. 1፡12፣ 15።

ለ. ጌታን እንደ ጸጋ መደሰት ያለው ጌታን ከሚወዱት ጋር ነው—ኤፌ. 6፡24፤ ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 1፡8።

ሐ. ጌታን ከመለኮታዊው ባሕሪው ጋር እንደ ጸጋ መደሰታችን፣ የእርሱን ክቡር እና እጅግ ታላቅ የሆኑትን ተስፋዎቹን ሁሉ የሚያካትተውን የእርሱን የጸጋ ቃል በመቀበላችን እና በእርሱ የጸጋ ቃል ውስጥ በመኖራችን አማካኝነት ነው—ሐዋ. 20፡32፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ ኤፌ. 6፡17-18።

**III. ወደ እኛ የሚመጣውን ጸጋ በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የነበሩት ነቢያት ተነበዩ—1 ጴጥ. 1፡10፦**

ሀ. በብሉይ ኪዳን ነቢያት ውስጥ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ክርስቶስ ለእኛ ጸጋ ለመሆን በተሠግዎው መምጣቱን በተመለከተ፣ በስብዕና ኑሮውና በስቅለቱ የነበረውን መከራውን በተመለከተ እና በትንሣኤው፣ በዕርገቱ፣ ሁለተኛ በመምጣቱና የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን በእኛ ላይ ይተገበር ዘንድ በመንገሡ ያሉትን ክብሮቹን በተመለከተ ለነቢያቱ ግልጽ አደረገላቸው—ቁ. 5፣ 9-10፤ ተዛ. መዝ. 22፤ ኢሳ. 53፤ ዳን. 9፡26።

ለ. ምንም እንኳን የክርስቶስ መንፈስ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል እና ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር በአዲስ ኪዳን ዘመን ቢዋቀርም (ዮሐ. 7፡39፤ ሮሜ 8፡9-11) የመንፈስ አገልግሎት ዘላለማዊ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ ዘላለማዊው መንፈስ ነው (ዕብ. 9፡14)።

ሐ. የክርስቶስ መንፈስ፣ በዘላለማዊው አገልግሎቱ የአዲስ ኪዳን አማኞች የነፍሳቸው መዳን ወደሆነው በመንግሥቱ ዘመን ወዳለው የጌታ ደስታ ይገቡ ዘንድ፣ የክርስቶስን ለሁሉ እንደሚበቃ እና ገደብ እንደሌለው የእግዚአብሔር ሙሉ ድነት ጸጋ ወደ አዲስ ኪዳን አማኞች መምጣት ግልጽ እያደረገላቸው በብሉይ ኪዳን ነቢያት ውስጥ ነበር—ዮሐ 1፡17፤ ዕብ. 10፡29፤ 1 ጴጥ. 1፡9፤ ማቴ. 25፡21፤ 23።

መ. የክርስቶስ መንፈስ የእግዚአብሔርን ሙሉ ማዳን እንደ ጸጋ በሁለት መንገዶች ይተገብራል፦ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ትንቢት እና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ስብከት—1 ጴጥ. 1፡10-12፤ ተዛ. ራእ. 2፡7።

**IV. አማኞች ተስፋቸውን ፈጽመው የሚያደርጉበት ጸጋ ወደ እነርሱ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ነው—1 ጴጥ. 1፡13፦**

ሀ. በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ወደ እኛ የሚመጣው ጸጋ እንደ የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን መጠናቀቅ የነፍሳችንን መዳን ያመለክታል—ቁ. 5፣ 9-10፦

1. በክርስቶስ የተሰጠን ጸጋ ለእኛ የተሰጠን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነበር—2 ጢሞ. 1፡9፤ ቲቶ 2፡11።
2. በመጀመሪያ የነበረው እግዚአብሔር፣ ሰው ይቀበለው፣ የራሱ ያደርገው እና ይደሰተው ዘንድ በጊዜ ውስጥ እንደ ጸጋ ሥጋ ሆነ—ዮሐ. 1፡1፣ 14፣ 16-17።
3. ሁሉን እንዳካተተ፣ ሕይወት-እንደሚሰጥ እና በውስጣችን እንደሚያድረው መንፈስ የተጠናቀቀው በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ከመንፈሳችን ጋር ያለ የጸጋ መንፈስ ሆኗል—1 ቆሮ. 15፡45፤ 2 ቆሮ. 3፡17፤ ዕብ. 10፡29፤ ገላ. 6፡18፤ ፊልጵ. 4፡23።

ለ. ዕለት ዕለት ባለማቋረጥ የጸጋ ተቀባዮች እንሆን ዘንድ ክፍት መያዣ ዕቃዎች መሆን እና በዚህም ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ እና ፍጹም በሆነ መልኩ ተስፋችንን ማድረግ አለብን—ሮሜ 5፡17፤ 1 ጴጥ. 1፡13።

V. **በ 1ኛ ጴጥሮስ 2፥19-20 "በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና (ጸጋ)" የሚያመለክተው የመለኮታዊውን ሕይወት በውስጣችን ማነሳሳት እና በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ዓይኖች መለኮታዊው ሕይወት በባሕሪያችን ምስጋና የተሞላና ተቀባይነት ያለው ሆኖ በኑሯችን መገለጡን ነው፦**

   ሀ. ጸጋ፣ ለድሰታችን በሂደት እንዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ የውስጥ ተነሳሽነታችን እና ከእግዚአብሔር ጋር ባለን የቅርብ ኅብረትና ለእግዚአብሔር ባለን ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ደግሞ ውጫዊ መገለጣችን ይሆናል፤ ጸጋ እንዴት እንደሚኖረን፣ ማለትም ጸጋን መውሰድን፣ ጸጋን የራስ ማድረግን፣ ጸጋን መጠቀምን እና ጸጋን መተግበርን ሁላችንም መማር አለብን—ዕብ. 12፥28።

   ለ. በሂደት ያለፈውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ ጸጋ መቀበላችን እና መደሰታችን በቅዱስ ኑሯችን እና በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎቻችን በሚታይ መልኩ ለሌሎች የሚገለጥ ይሆናል—ሐዋ. 11፥23።

   ሐ. በአምላክ-ሰው ኑሮው መሠረት እንደ ሞዴላችን የክርስቶስ ርቢ፣ ፎቶ ኮፒ እንሆን ዘንድ በመከራዎች መካከል ሁሉ ክርስቶስን እንደ ጸጋ ለመደሰት እና ለመግለጥ ተጠርተናል—1 ጴጥ. 2፥20-21።

VI. **የሕይወት ጸጋ የብርቱዎቹም ሆነ የደካሞቹ አማኞች ሁሉ ርስት ነው—3፥7፦**

   ሀ. የሕይወት ጸጋ በመለኮታዊ ሥላሴው እግዚአብሔር ሕይወታችን እና የሕይወት አቅርቦታችን መሆኑ ነው—አብ እንደ የሕይወት ምንጭ፣ ወልድ እንደ የሕይወት መንገድ እና ከወልድ እና ከአብ ጋር ለእኛ እንደ ጸጋ በውስጣችን የሚፈስ የሆነው መንፈስ እንደ የሕይወት ፍሰት—1 ዮሐ. 5፥11-12፤ ዮሐ. 7፥38-39፤ ራእ. 22፥1።

   ለ. የሕይወትን ጸጋ ለመውረስ ወራሾች ነን፣ የሕይወትን ጸጋ ለመያዝም መያዣ ዕቃዎች ነን—1 ጴጥ. 3፥7፤ ኤፌ. 1፥14፤ 2 ቆሮ. 4፥7።

VII. **ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ጸጋ ብልጥግናዎች በተለያየ መልኩ በቅዱሳን አማካኝነት ከአንዳቸው ወደ ለሌላቸው መገልገሉን ነው—1 ጴጥ. 4፥10፦**

   ሀ. ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ የበለጠገ የሕይወት አቅርቦት ነው፣ ይህም በብዙ ገጽታዎች ወደ እኛ ውስጥ የተገለገለው ሦስታንዱ አምላክ ነው—2 ቆሮ. 13፥14፤ 12፥9።

   ለ. እንደ የእግዚአብሔር ንግግር የጸጋ ቃላትን በመናገር እና እግዚአብሔር እንደ አቅርቦት በሚሰጠን በጸጋ ብርታት እና ኃይል በማገልገል የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች መሆን ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 4፥10-11፤ ሉቃስ 4፥22፤ ኤፌ. 3፥2፤ 4፥29።

VIII. **እግዚአብሔር ለትሑታን ጸጋን ይሰጣል፣ ትዕቢተኞችን ግን ይቃወማል—1 ጴጥ. 5፥5፦**

   ሀ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት እግዚአብሔርን እንደ ጸጋ-ሰጪው እንደሰተው ዘንድ እርስ በርሳችን ባለን ግንኙነት ትሕትናን መታጠቅ ያስፈልገናል—ተዛ. ዮሐ. 13፥3-5።

   ለ. ትሕትና ከሁሉ አይነት ጥፋት ያድነናል፣ የእግዚአብሔርንም ጸጋ መቀበል ያስችላል፣ ትዕቢት ግን የሞኞች ሁሉ ሞኝ ያደርገናል—ያዕ. 4፥6፤ መዝ. 138፥6፤ ምሳ.29፥23።

   ሐ. እግዚአብሔር በፍቅር እና በታማኝነት ስለእኛ ስለሚያስብ ሁሉን ቻይ ከሆነችው እጁ ሥር በእርሱ ቅጣት ውስጥ ትሑት ለመደረግ፣ ዝቅ ለመደረግ እና ሕይወታችንን ከሚሳሳላቸው ጉዳዮቹ ጋር በእግዚአብሔር ላይ ለመጣል ፈቃደኞች መሆን አለብን—1 ጴጥ. 5፥5-7፤ ተዛ. መዝ. 55፥22።

IX. **"የጸጋ ሁሉ አምላክ"—ወደ ዘላለማዊው ክብሩ አማኞችን የጠራው እርሱ—በመከራዎቻቸው ሁሉ ፍጹማን ያደርጋቸዋል፣ ያጸናቸዋል፣ ያበረታቸዋል፣ ያደላድላቸዋል፤ ይህ "ጸጋ ሁሉ" አማኞች ሊገቡበት የሚገባ እና የሚቆሙበት "እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ" ነው—1 ጴጥ. 5፥10፣ 12።**

X. **እውነተኛው የእግዚአብሔር ጸጋ ከጌታችንና ከአዳኛችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ጋር አማኞች አሁንና እስከ ዘላለም ድረስ ወደ ክብሩ ሊያድጉበት የሚገባ ጸጋ ነው፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ የጻፈው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት እና በእግዚአብሔር ጸጋ በኩል እንደሆነ በማመልከት ይህ የጽሑፎቹ መደምደሚያ ቃል ነው—2 ጴጥ. 3፥18።**